**ORAC SP/03 (REV 1)**

<u>ሰብሲዳሪ ከለላ ለማመልከትን አስመልክቶ ለስደተኞች ጠቃሚ ማስታወቂያ</u>

1. በአውሮፓ ህብረት የፍትህ ፍርድ ቤት መመሪያ የH. N. v. የፍትህ፣ የእኩልነት እና የህግ ማሻሻያ፣ አየርላንድ እና ጠቅላይ ጠበቃ፣ የአውሮፓ ህብረት (ሰብሲዳሪ ከለላ) መመሪያ 2013 (S.I. ቁጥር. 426 የ 2013) ተሻሽሏል፡፡

2. የአውሮፓ ህብረት (ሰብሲዳሪ ከለላ) (ማሻሻያ) መመሪያ 2015 (S.I. ቁጥር. 137 የ 2013) የፍርድ ቤቱን መመሪያ በማሟላት ህጋዊ ተፈፃሚነት አላቸው፡-

   - ማንኛውም አዲስ በስደተኝነት ደረጃ የሚያመለክት ሰው ሁሉ በስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ቢሮ (ORAC) ለሰብሲደሪ ከለላም ማመልከት ይችላል፡፡

   - ማንኛውም በስደተኝነት ደረጃ አመልክቶ በመጠባበቅ ላይ ያለ ሰው ሁሉ በስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ቢሮ (ORAC) ለሰብሲደሪ ከለላም ማመልከት ይችላል።

3. የሰብሲደሪ ከለላ ማመልከቻዎች በአውሮፓ ህብረት (ሰብሲደሪ ከለላ) መመሪያ፣ 2013 (S.I. ቁጥር. 426 የ 2013) (እንደተሻሻለው) መሰረት በ ORAC ይወሰናል፤ እና የግለሰቡ ማመልከቻ በፍትህና እኩልነት ሚኒስተር ተቀባይነቱ ይጣራል።

4. **የ2015ቱ መመሪያ ያካተታቸው ምንድን ናቸው?**

**እርስዎ ለሰብሲዳሪ ከለላ አዲስ አመልካች ከሆኑ፡-**

የ2015 መመሪያ ማንኛውም አዲስ በስደተኝነት ደረጃ የሚያመለክት ሰው ሁሉ ለሰብሲደሪ ከለላም ማመልከት እንዲችል ያደረገ ሲሆን ይህም የግለሰቡ ማመልከቻ በስደተኝነት ደረጃ በፍትህና እኩልነት ሚኒስተር ተቀባይነቱ በኮሚሽነሩ ተጣርቶ ይወሰናል። በዚህ ረገድም፣ በመቀጠልም ኮሚሽነሩ በ2013 መመሪያ (በተሻሻለው) ከሰብሲደሪ ከለላ የአመልካቹ ቃለመጠይቅ በማስከተል፣ ስለማመልከቻው የተደረገውን ምርመራ በጹሁፍ ሪፖርት ያዘጋጃል። ኮሚሽነሩም ለፍትህና እኩልነት ሚኒስተር አመልካቹ ለሰብሲደሪ ከለላ ብቁ/የሚያሟላ መሆኑን እና አለመሆኑን ምክረሃሳብ ያቀርባል።

**እርስዎ ለሰብሲዳሪ ከለላ ነባር አመልካች ከሆኑ፡-**

የ2015 መመሪያ ማንኛውም  በስደተኝነት ደረጃ አመልክቶ በመጠባበቅ ላይ ያለ ሰው ሁሉ ለሰብሲደሪ ከለላም ማመልከት እንዲችል ያደረገ ሲሆን ይህም የግለሰቡ ማመልከቻ በስደተኝነት ደረጃ በፍትህና እኩልነት ሚኒስተር ተቀባይነቱ በኮሚሽነሩ ተጣርቶ ይወሰናል። በዚህ ረገድም፣ በመቀጠልም ኮሚሽነሩ በ2013 መመሪያ (በተሻሻለው) ከሰብሲደሪ ከለላ የአመልካቹ ቃለመጠይቅ በማስከተል፣ ስለማመልከቻው የተደረገውን ምርመራ በጹሁፍ ሪፖርት ያዘጋጃል። ኮሚሽነሩም ለፍትህና እኩልነት ሚኒስተር አመልካቹ ለሰብሲደሪ ከለላ ብቁ/የሚያሚላ መሆኑን እና አለመሆኑን ምክረሃሳብ ያቀርባል።

5. ከላይ ለተገለጹት ሰዎች፣ የተሟላ ORAC ፎርም SP/04 በማስገባት ለሰብሲደሪ ከለላ ማመልከት የሚቻል ሲሆን [ማመልከቻዎች በአውሮፓ ህብረት በመመሪያ 3A(1) (ሰብሲደሪ ከለላ) መመሪያ 2013 (እንደተሻሻለው) ለሰብሲደሪ ከለላ ድንጋጌ] ሆኖ፡-
   - በአካል በመቅረብ፤ ስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ቢሮ፣ ቲምበርለይ ሐውስ፣ 79-83 ለወር ማውንት ጎዳና፣ ደብሊን 2፣

     <u>ወይም</u>

   - በፖስታ ለORAC ደንበኞች አገልግሎት ማእከል፣ ቲምበርለይ ሐውስ፣ 79-83 ለወር ማውንት ጎዳና፣ ደብሊን 2፣ ማመልከት ይቻላል።

6. እርስዎ የሰብሲደሪ ከለላውን ካመለከቱ በኋላም የORAC ፎርም SP/05 በመሙላት ተጨማሪ መረጃ መስጠት ይችላሉ (ከማመልከቻው ጋር የተያያዘ ተጨማሪ መረጃ በ3A(1) የአውሮፓ ህብረት መመሪያ (ሰብሲደሪ ከለላ) መመሪያ 2013 (እንደተሻለው) የሰብሲደሪ ከለላ ድንጋጌ መሰረት እና ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ ማስገባት)። ሚኒስትሩ የስደተኛነት ደረጃ ማሳወቂያውን ከላከ በኃላ ተጨማሪ መረጃው ካመለከቱበት ቀን እስከ 15 የስራ ቀናት ለኮሚሽነሩ ሊሰጥ ይችላል።

7. የ2013 እና 2015 መመሪያዎች ሙሉ ሰነድ ከስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ድህረ-ገጽ  http://www.ORAC ላይ ማግኘት ይቻላል

የስደተኞች ማመልከቻ ኮሚሽነር ቢሮ

ሚያዚያ 20 2015 እ.ኤ.አ